# ‹‹ስራ እንጂ ወሬና አሉባልታ ተከትለን አንሂድ››

# የመንግስት ወቅታዊ መልዕክት

ሠይፉ ደርቤ 8/4/12

‹‹አሉባልታ ተከትለን አንሄድም የሚያወራ ያውራ፣ መንግስት ስራ ላይ ነው...›› የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትር አቶ በረከት ስምዖን በመንግስት የእቅድ አፈፃፀምና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጤንነት ዙሪያ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ የገለፁት ነው፡፡

ሚኒስትሩ ይህን ያሉት ለምንድን ነው? ምን አይነት አሉባልታና አደናጋሪ የፈጠራ ወሬዎች ሲንሸራሸሩ ሰነበቱ? ብለን እንጠይቅ፡፡ በተለይ የሰሞኑ መነጋገሪያ ከሆኑት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የጤንነት ጉዳይ በስተጀርባ እነማን ምን እያቀነቀኑ ነው ከሚለው ጀምሮ ግባቸው ምን እንደሆነም እንመርምር፡፡

በሀገራችን የተለያዩ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሲንሸራሸሩ የነበሩ አሉባልታዎች ከታህሪር አደባባይ አመፅ ወይም ከአልጄሪያው ወጣት ሙሃመድ ቡአዚዝ ራስን የማቃጠል ክስተት ወዲህ የተጀመሩ አይደሉም፡፡ ምንም እንኳ እነዚህን ሁኔታዎች እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የወሬ ዘመቻው ቢጠናከርም በእያንዳንዱ የልማትና ዴሞክራሲ ጉዳይ በመንግስት የሚወሰድ እርምጃን እየተከተሉ ሲፈበረኩ የነበሩ ወሬዎችና የሁልጊዜም ሟርቶች አብረውን አሉ፡፡

ሟርቶቹ በሀገራችን አዲስ ስርዓት ከተበጀ ጀምሮ መድብለ ፓርቲያዊ ስርዓቱ ባስገኘው የፖለቲካ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ የመደራጀት መብት ከሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጀምሮ፣ በውጭ ሀገር የፖለቲካ ጥገኞች ነን ብለው ራሳቸውን እስከሚጠሩት ሲቀነቀኑ ቆይተዋል፡፡

ኢትዮጵያ አበቃላት፣ ተበታተነች ከሚል ወሬ አንስቶ የህዝቡ መድረሻ ወዴት እንደሆነ እስከሚጠይቁ የግላጭ መግለጫና ዘገባ ድረስ ተመልክተናል፡፡

በዚህ ሁሉ ሟርት ውስጥ ቢሆንም ታዲያ አበቃላት ስትባል የነበረችው ሀገርና ህዝብ በማያበቃ የልማትና እድገት ትግል ውስጥ ተጠምደው የድህነትና ኋላቀርነት ታሪካቸውን ለመለወጥ ተግተዋል፡፡ በዚህ ሂደት እግጅ በርካታ አንፀባራቂ ውጤቶችን አስመዝግበዋል፡፡ ይኸው ወዳጅም ጠላትም የሚመሰክርለት ሆኗል፡፡ በመሰረተ ልማት፣ በጤናና ትምህርት ኢትዮጵያ ወደፊት እየተራመዱ ካሉ ሀገሮች ግንባር ቀደም መሆን መጀመሯ በተደጋጋሚ ጊዜ መገለፁ የዚሁ አንድ አስረጂም ነው፡፡

የኢትዮጵያ የልማትና ዴሞክራሲ ጉዞ ፈተናዎች የሚጀምሩት ሀገሪቱ ከምትከተለው ርዕዩተ ዓለም በመነጨም ነው፡፡ የሀገሪቱ መስመር የህዝቡን ነባራዊ ሁኔታና የረጅም ዘመናት ቁጭት ግምት ውስጥ ያስገባ በመሆኑ ለኒዮ ሊበራሉ ሃይል የሚመች አልሆነም፡፡ ሀገሪቱ ማንም እንዳሻው ገብቶ ለራሱ የሚፈጥረው፣ ጣልቃ ገብቶም የሚያሽከረክረው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምህዳርም አላፀናችም፡፡

በዚህም ምክንያት በህዝብ ልማትና ጥቅም ላይ ያነጣጠረው የትኛውም የሀገሪቱ መሰረተ ልማት በኒዮ ሊበራል ካምፕ ውስጥ በመሸጉ ሃይሎች የሚወደድበት እድል የለውም፡፡ ይህ ሃይል ከሀገሪቱ የልማት አቅጣጫ በተፃራሪ ለቆሙ ሃይሎች ምቹ ሆኖ መቀጠሉና የሚፈጥሩትን አሉባልታ ሳይመረምር በማስተጋባት ስራ መጠመዱ ለዚሁ ነው፡፡ የዚሁ ሀይል ፅንስና ውላጅ የሆነው በስም የመብትና የሙያ ተከራካሪ ቡድን ነን ባይ ባለ አጀንዳ፣ የማያቋርጥ ውዥንብር ማሰማቱ ከዚሁ በመነጨ ነው፡፡

ያም ሆኖ የኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቅጣጫ በህዝቡና በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተግዳሮቶቹን ተቋቁሞ ማሸነፉን ቀጥሏል፡፡ ኢትዮጵያ አሉባልታውን ተከትላ ስራ ለፈቱ ባለወሬዎች ምላሽ በመስጠት ከመጠመድ ይልቅ በማያልቀው የልማት ጉዳይ መጠመዷን በተግባር እያሳየች ነው፡፡

እያንዳንዱ የልማት ተግባር በተጠናከረ ቁጥር የህዝቡ ትኩረት በዚሁ ላይ እንደሚያተኩር፣ በሀገሩ መንግስት ላይ የጠነከረ አቋም በመያዝ በጋራ ጠላቱ ድህነት ላይ በመዝመት ብቻ እንደሚጠመድ የሚያውቁ የጥፋት ሃይሎች የታላቁን ህዳሴ ግድብ መጀመር እንኳ እንደ አመፅ አቅጣጫ ማስቀየሪያ ስልት አድርገው በወረደ የአስተሳሰብ ደረጃ ገልፀውታል፡፡

የ80 ሚሊየን ህዝብ ሀገር በሆነችው ኢትዮጵያ መላው ህዝብ ከዳር ዳር ተረባርቦ ከዘመናት ሀገራዊ ውርደት እወጣለሁ ብሎ አቋም በያዘበት የአባይ ጉዳይ ‹‹ግድቡ ወቅታዊ አይደለም የሚሉ ወገኖችና እስካሁን ለምን ዘገየ›› በሚሉ የአንድ ስብስብ ሁለት ጥላዎች ህዝቡን ግራ ሊያጋቡ ሞክረዋል፡፡

በሀገሩ ልማት ልዩነት አይገድበኝም ብሎ አቋም የያዘውን ዳያስፖራ ለግድቡ ቦንድ እንዳይገዛ፣ ድጋፍም እንዳያደርግ ታላቅ ዘመቻ ቢከፍቱም ልማቱን ሊያስቆሙ፣ የፀረ ድህነት አጀንዳውን ሊገቱ ያልቻሉ የጥፋት ቡድኖች ትዝብት ውስጥ ወድቀዋል፡፡ ህዝቡ ታሪካዊ ሃላፊነቱን በመወጣት እኔም ለመጪው ትውልድ አሻራዬን አኖራለሁ ብሎ የድርሻውን በመወጣት አሳፍሯቸዋል፡፡

በዚህ ርብርብ ገጠር ከከተማ ሳይለይ፣ በሀገር ውስጥ ያለው በውጭ ካለው ሳያንስና ሳይነጠል ለጋራ ልማቱ ያለውን አቋም በተግባር አረጋግጧል፡፡ ያልተሞከረው ተሞክሮ፣ ያልታሰበው በተግባር ውሎ ለአመፅ ተሰባሰብ በሚል ጥሪ የቀረበለት ህዝብ ለልማት ሆ ብሎ የጥፋት ሃይሎችን አንገስ ማስጎንበስ ችሏል፡፡

በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን እያንዳንዱ ልማት መንግስት ስምና ዝና ሊሸምትበት ነው በሚል መጥፎ ጥንውትና ስሌት የሀገሪቱን ገፅታ እያጠየሙ የህዝብ ተሳትፎ እንዳይኖር እስከ መቀስቀስ የደረሰ የማደናቀፍ ዘመቻዎች እየፈፀሙ ያሉ ሃይሎች ሙከራ ብዙ ነው፡፡

የመሬት ሊዝ አዋጅን በሚመለከት የወጣውን አዋጅ ህዝቡን ሜዳ ላይ የሚያስቀር፣ ቤት ንብረትን የሚወርስ፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነትን የሚፈጥርና ገዥው ፓርቲ የዘላለም የምርጫ ካርድ የሚገዛበት ነው ያሉ እንደ መድረክ አይነት ፓርቲዎችን አይተናል፡፡

ከቤታቸው በሰላም ወጥተው መንገድ ላይ በሽብር ጥቃት ጭዳ ሆነው የቀሩ ብዙዎችን አይተው እንዳላዩ በመሆን ሽብርተኝነት በሀገራችን የለም በሚል አይናቸውን በጨው ታጥበው በአደባባይ የተናገሩ ቡድኖችንም ታዝበናል፡፡ ከመረሳት ብድን ወይም የተወሰነ ደጋፊ ባገኝ ብሎ ቀልብ ለመሳብ የሞከረው መኢአድ አክራሪነት በኢትዮጵያ የለም ብሎ አስገርሞናል፡፡

በሽብር ተግባር በሀገርና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሱ ሃይሎች መከሰስ ፖለቲካዊ ስዕል እንዲኖረው ሲወተውቱ የሰማናቸው የሀገር ውስጥና የውጭ የስም ተሟጋቾች ከሃቅ ሲላተሙ አይተናል፡፡ ሽብርተኝነትን ለመከላከል የወጣውን የፀረ ሽብር አዋጅ እንደ አፈና መሳሪያ ቆጥረው፣ በሽብር አንድ ነፍስ እንዳልጠፋ ገልፀውና ክደው ‹ሂዩማን ራይትስዎች› አፋችንን ከመዘጋት ያድነው ያሉ፣ በህዝብ ላይ ሳይሆን ጫንቃቸውን በውጭ ሀይሎች ላይ የመሰረቱ ቡድኖች እንዴት እየተንቀሳቀሱ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

በጠንካራ ፖለሲና አፈፃፀም እየተገኘ ያለውን ውጤት ወደ ጎን ብለው ከእውነታ ባፈነገጠ መልኩ የሀገሪቱን ገፅታ ጥላሸት ለመቀባት የረሃብ ድርሰት ደርሰውና የፈጠራ ረሃብ አዋቅረው በአደባባይ ብቅ ያሉ ፖለቲከኞች መመልከታችንም የቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ሟርቱ ከዚህም በላይ ነው፡፡…

መንግስት ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎትና ጥቅም መሳካት አንፃር እያካሄደ ያለውን ፈጣን ልማትና እድገት እንዳስቀጠለው ሁሉ አሁንም ይህ ሟርትና የበሬ ወለደ ወሬ ቀጥሏል፡፡ የሀገራችንን የፍትህ ስርዓት እንዳሻቸው ለማድረግ የሚፈልጉ ሀይሎች በተግባር ባይችሉም በቃል ጣልቃ ገብተው የፍትህ ስርዓታችንን ሊዘውሩት ሞክረዋል፤ ህጎቻችንን ሊያረቅቁም ፈልገዋል፡፡ የኢትዮጵያ የልማት

ጥም በምፅዋት ይሞላ ይመስል የሚያስፈልገን የረድኤት ድርጅቶች እንጂ አብዝተን የምናለማው ልማት እንዳልሆነም በተዘዋዋሪ ገልፀውልናል፡፡

በሀገር ውስጥ ያሉ ጨለምተኞችና ዳያስፖራው ውስጥ በፖለቲከኛ ጥገኝነት ስም ራሳቸውን የሚገልፁ ሃይሎች ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፣ ሁሌም የሚያልሙትን የአመፅና ብጥብጥ ተግባር አስቀረብን ብለው ይወቅሳሉ፤ የአካባቢ ተቆርቋሪ ሆነው ለመታየት የሚከጅሉ የውጭ ሃይሎች ደግሞ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ንትርክ ውስጥ ሊከተን የሚችል አጀንዳ ቀርፀው ልማታችን ከባቢያዊ ጉዳት እንዳለው ይሰብካሉ፡፡

እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ ወገኖችም ሌላ የርዕዩተ ዓለም ጦርነት ከፍተውብናል፡፡ ህግ የማውጣት መብትና ስልጣን የሉዓላዊ ሀገሩ ባለቤት በሆነው ኢትዮጵያዊ መሆኑን ይኮንናሉ፡፡ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስም በተቋቋሙ ረድኤት ድርጅቶች በኩል ፖለቲካችንን ሊዘውሩም ይፈልጋሉ፡፡

በህገ መንግስታችን በግልፅ የተቀመጠውን የዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብት ወደ ጎን ብለው ስለ ዴሞክራሲ ሊያስተምሩን፣ ለዚህም መብት አለን ሲሉም ይወቅሳሉ፡፡ ዓለም እየተገለገለበትና እነሱም እየተዳኙበት ያለው የፀረ ሽብር ህግ እኛ ሀገር ላይ ሲደርስ እንደማይሰራ አስረግጠውም ይነግሩናል፡፡

በነፃ ፍርድ ቤትና በህግ የተፈፀመን ዳኝነት የአስፈፃሚው አካል ጣልቃ ገብነት አለበት ብለው ሳይጨርሱ ከፍርድ በፊት ጣልቃ ገብተው በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች ነፃነት ይሰጣሉ፤ ህጋዊውን እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ስዕል ያለብሳሉ፡፡

ይሄ ሁሉ የበሬ ወለደ ፈጠራና የሀሰት ውንጀላ የኢትዮጵያን ልማትና የፍትህ ስርዓት ጉዞ አላቆመውም፡፡ ይልቁንም በህዝብ የተመረጠው መንግስት ከመራጩ ህዝብ ጋር በመሆን ታላቁን እቅድ በታለመለት ሁኔታ ለማሳካት ርብርብ ይዟል፡፡ ከአምስት ዓመቱ እቅድ የሁለት ዓመቱን

አፈፃፀም መገምገምም ጀምሯል፡፡ በሁለቱ ዓመት አፈፃፀም የተሻለውን ይበልጥ ለማስቀጠል፣ የደከመውን ለማሻሻል ሰፊ የልማት ዘመቻ ውስጥ ገብቷል፡፡

የከተማው ልማት መሰረት ገጠሩ በአርሶ አደሩ የልማት ተሳትፎ ምን እያከናወነ፣ እንዴትስ እየተንቀሳቀሰ ነው ብሎ አፈፃፀሙን እየጎበኘ ያለው አስፈፃሚ ከልማት ሀይሉ ጋር በስራ እንደተጠመደ ሁሉ ብዙ ሞቶችና መተራመሶችን የሚሹ አሉባልተኞች አሁንም አሉባልታቸውን ቀጥለዋል፡፡

ሀገሪቱ ላለፉት 20 ዓመታት እየተመራችበት ያለው ህገ መንግስት ስለ መንግስት አስተዳደርና ስልጣን ምን እንደሚል ሳያነቡ የተለያዩ ሟርት ተኮር ወሬዎችን ኃላፊነት በማይሰማው መልኩ በማሰራጨትም ላይ ናቸው፡፡ የሟርቱ ዓላማና ግብ በየትኛውም መመዘኛ ውድቀትን መሻት ሆኖ መታየቱ ደግሞ እነዚህ ወገኖች ለሀገራችንም ሆነ ለህዝባችን ምንም ራዕይና ተስፋ ያልሰነቁ መሆኑን እንድናረጋግጥ ያስችለናል፡፡

እነዚህ ወገኖች በዚህ ተግባር መጠመዳቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሳየው የተሻለ ነገር አማራጭ ሃሳብ ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የመረዳት እድል መስጠት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ማፈራረስን ብቻ አጀንዳ ማድረጋቸውን፣ ቢያፈርሱ እንኳ ለመሰብሰብ አቅም የሌላቸው በታታኝ መሆናቸውንም ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ህዝቡ ቀድሞ አውቋቸዋል፤ በሀገሩ ጉዳይ ክፍተት እንዳይፈጥር እድል ነስቷቸዋል፡፡

የዚሁ አንዱ ማሳያ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማያውቅ መልኩ ሃይማኖቶች ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት እምነታቸውን ማስኬድ መቻላቸውን ተፃርረው በእምነት ሽፋን ብጥብጥና ኹከት ለመፍጠር ያደረጉት ጥረት መክሸፉ ነው፡፡ መንግስት የኃይማኖት ነፃነት እንዲከበር ህገ መንግስታዊ ዋስትና በመስጠት ጭምር ያረጋገጠውን የዜጎች መብት በአክራሪ አስተሳሰብ ተጭነው፣ በአንድ አመለካከትም ቀይደው ኃይማኖታዊ መንግስት ለማምጣት ያደረጉት እንቅስቃሴም መጋለጡ ነው፡፡

እነዚህ ኃይሎች መንግስትና ኃይማኖቶች ከ20 ዓመታት በላይ ያፀኑትን መተማመን በጥርጣሬና ስጋት ለመቀየር ቢረባረቡም የሀገሩ እና የእምነቱ ባለቤት የሆነው ህዝብ በአደባባይ አውግዟቸዋል፡፡ የእምነት ነፃነቱ መሰረት የሆነውን ህገ መንግስት እንደሚያከብርና እንደሚያስከብርም አረጋግጦላቸዋል፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትሩ አቶ በረከት ስምዖን መንግስት ከአሉባልታ ጋር አብሮ እንደማይከንፍና ከዚያ ይልቅ የህዝቡንና የሀገሪቱን ፍላጎት በሚያሟሉ በርካታ የልማት ስራዎች መጠመዱን ከትላንት በስቲያ ለህዝቡ መግለፃቸው ከዚህም አኳያ ነው፡፡

በእርግጥም በአንዳንዶች በተለያዩ ማህበራዊ ድረገፆችና የፕሬስ ነፃነቱ ባስገኘው መብት የሚቀርቡ የበሬ ወለደ ፈጠራና ዘገባዎች የስራ ፈቶች አሉባልታ እንጂ ምንም ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ እነዚህኑ አስተሳሰቦች የሚያቀነቅኑ የውጪ ሃይሎችና ተምረናል ባይ ግለሰቦች የፖለቲካን ትርጉም ከህዝብ ጥቅም አንፃር ቢያጤኑትም መልካም ነው፡፡

ጭፍንነት በ‹ኮብል ስቶን› ጉዳይ ትዝብት ውስጥ የጣላቸውን ያህል በቀጣይ የሚፈጥሩትና አሁን እያቀነቀኑት ያለው ሟርትና አሉባልታ ሌላ ትዝብትና ጥላቻ ውስጥ እንዳይጥላቸው በእርግጥም መጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ ሚኒስትሩ አቶ በረከት ስምዖን በተለይ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጤንነት ጋር አያይዘው የሰጡት ማብራሪያ አሉባልተኞችን ከህፍረት የሚያድን ወቅታዊ መልዕክት ያዘለ ነው፡፡